የሰበር መ/ቁ 14057

ጥቅምት 30 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሀ ወርቅነህ

ስንዱ አለሙ

ሆሳዕና ነጋሽ

አሰግድ ጋሻው

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ነ/ፈጅ ኃይሉ ተሰማ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ጌታሁን ኃይሉ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

አመልካች ለሰበር ችሎት አቤቱታ ያቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 15313 ህዳር 25 ቀን 1996 ዓ.ም የዓመት ዕረፍት ክፍያን በተመለከተ በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረተው ከሌሎች ክፍያዎች ጋር የተጠራቀመ የ128 ቀናት የዓመት ዕረፍት በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈለው ነው፡፡ አመልካች የዓመት ዕረፍት ክፍያን አስመልክቶ በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 79 2 እና 5 መሠረት የተላለፈው የዓመት ፈቃድ የሚቀጥለው ሁለት ዓመት በላይ ሊራዘም አይችልም ተጠሪ የጠየቀው ክፍያ በሕጉ ከተሰጠው በላይ ስለሆነ ሊከፈለው አይገባም በማለት መከራከሩን የፍ/ቤቱ ውሣኔ ያሳያል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ /... የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 192/1/ሠ አዋጅ ቁጥር 64/68 የሆነውን በግልጽ የሻረው በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ አዋጅ ቁጥር 42/85 ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም የሚለው የተከሣሽ ክርክር ተቀባይነት የለውም፣ ስለሆነም በአዋጅ ቁ.42/85 በአንቀጽ 79/5/ ሥር በአንቀጽ 79/1 እና /2/ የተላለፈ የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ከሁለት ዓመት በላይ መራዘም እንደሌለበት የተደነገገ በመሆኑ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የከሣሽ 128 የእረፍት ቀናት ተቀንሶ አዋጁ በስራ ላይ ከዋለበት



ከጥር 12/85 ጀምሮ እስከተሰናበቱበት ጊዜ እስከ ጥር 28/86 ዓ.ም ያለው ጊዜ አንድ ዓመት ከአስራ ሶስት ቀናት የአመት ዕረፍት ክፍያ ብቻ በአንቀጽ 77/3/ መሠረት እንዲከፈል የሚል ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ ፍ/ቤቱም አዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 79/5/ የዓመት ዕረፍት ከሁለት ዓመት በላይ ሊተላለፍ አይችልም ሲል ሠራተኛው ከሁለት ዓመት በላይ ያጠራቀመው የዓመት ዕረፍት ካለ አይገባውም ማለቱ አይደለም፡፡ ይልቁንም በአዋጁ በቁጥር 77/5/ ላይ ያልወሰደው የዓመት ፈቃድ በጠቅላላ ታስቦ እንዲከፈለው ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የጠየቀው የዓመት ዕረፍት ክፍያ ሳይቀነስ እንዲከፈለው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔውን በመሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካች የከፍተኛ ፍ/ቤት መሠረታዊ የሆነ ሕግ ስህተት ፈጽሟል ሲል አቤቱታ ያቀረበው በዚህ ውሣኔ ነው፡፡ ታህሣሥ 19 ቀን 1996 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው ማመልከቻ በውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተሰርቷል ሲል የሚያቀርባቸው ክርክሮችም፣

- የተጠሪ የዓመት ዕረፍት በገንዘብ ተቀይሮ ይከፈለኝ ጥያቄ ከሥራ ከመሰናበታቸው ጥር 30/86 ዓ.ም በፊት የነበረና በተለይም አዋጅ በአንቀጽ 34/4/ ከሀ-ሠ መሠረት ያልተላለፈ በመሆኑ ሊጠየቅ አይገባም፡፡
- በአዋጅ አንቀጽ 79/2-3/ መሠረት ሠራተኛው ጠይቆ ወይም አሠሪው የሥራ ሁኔታ አስገድዶት የተላለፈ ለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የሌለ ከመሆኑም በላይ በዚሁ አንቀጽ 79/5/ በግልጽ እንደተቀመጠው በሁለቱ ስምምነት የተላለፈ የዓመት ዕረፍት ቢኖር እንኳን ከሁለት አመት በላይ ሊራዘም እንደማይችል በግልጽ ሰፍሯል፡፡ ተጠሪ በአዋጁ መሰረት የተላለፈ የዓመት ዕረፍት ያላቸው ለመሆኑ ያልገለጹ ከመሆኑም በላይ አንቀጽ 79/5/ ከሁለት አመት በላይ ሊተላለፍ እንደማይችል በግልጽ የደነገገውን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባለመቀበል በአዋጅ አንቀጽ 77/5/ በሙሉ በገንዘብ ተቀይሮ ይከፈላቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚሉ ናቸው፡፡

አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ ታዞ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሠረት ሚያዚያ 28 ቀን 1996 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ በመልሱም የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ የህግ ስህተት እንደሌለበት በመግለጽ እንዲፀና ጠይቋል፡፡ አመልካቹም የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

በዚህ ጉዳይ ተመርምሮ ሊወሰን የሚገባው ዋናው የክርክር ጭብጥ አንድ ሠራተኛ የሥራ ውሉ ሲቋረጥ ያልተጠቀመበትን የዓመት ዕረፍት ቀናት ሁሉ የጊዜ ገደብ ሳይኖረው በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈለው ይገባል ወይ? የሚለው ጭብጥም ይታያል፡፡

በቅድሚያ ግን አመልካች የተጠሪ የዓመት ዕረፍት በገንዘብ ተቀይሮ ይከፈለኝ ጥያቄ አዋጅ ቁ. 42/85 ከመውጣቱ በፊት የነበረ መብት ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 64/68 መሠረት መታየት ይገባዋል ሲል የሚያቀርበውን ክርክር ተመልክተናል፡፡ ተጠሪ ክሱን ያቀረበው ግንቦት 14 ቀን 1990 ዓ.ም አዋጅ ቁጥር 42/85 በሥራ ላይ እያለ ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 64/68 በአንቀጽ 192/ሠ/ እንደተሻረ ተገልጿል፡፡ አዋጅ ቁጥር 64/68 በኋላኛው አዋጅ በስራ ላይ ከዋለ በኋላ ተፈፃሚ የሚሆነው በአዋጅ ቁጥር 42/85 በቁጥር 191 እንደተደነገገው አዋጅ ቁጥር 64/68 በሥራ ላይ እያለ ክሱ መታየት ጀምሮ ቢሆን ነበር፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የተሻረውን አዋጅ ቁጥር 64/68 ተፈፃሚ ለማድረግ መታየት ያለበት የኋላኛው አዋጅ ሲተካ ሥራ ላይ ሲውል ጉዳዩ በቀድሞው አዋጅ መታየት የጀመረ መሆን አለመሆኑን እንጂ መብቱ የተገኘበትን ጊዜ አይደለም፡፡ ከላይ እንደተገለፀው ተጠሪ ክሱን ያቀረበው አዋጅ ቁጠር 42/85 በሥራ ላይ እያለ በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ተፈጻሚ የሚሆነው ይኸው አዋጅ ቁ.42/85 ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች የአዋጁን ተፈፃሚነት በተመለከተ የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

በመቀጠልም አንድ ሠራተኛ የሥራ ውሉ ሲቋረጥ ያልተጠቀመበትን የዓመት ዕረፍት ሁሉ ያለጊዜ ገደብ በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈለው ይችላል ወይ? የሚለውን ዋና ጭብጥ እንመለከታለን፡፡



ይህን ጭብጥ ለመመርመር በቅድሚያ የዓመት ፍቃድን ምንነትና አስፈላጊነት መመልከት ተገቢ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 42/85 ከአንቀጽ 76-78 ካሉት ድንጋጌዎች የአመት ፈቃድ ለሠራተኛ ከክፍያ ጋር የሚሰጥ የስራ ቀናት የዕረፍት ጊዜ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በአዋጁ ቁጥር 13/4/ መሠረት ሠራተኛው ለሥራ ብቁ በሆነ የአእምሮና የአካል ሁኔታ በስራ ላይ መገኘት ይጠበቅበታል፡፡ የአመት ዕረፍት ከሚሰጥባቸው ምክንያቶች አንዱና ዋነኛው ሠራተኛው ይህን የሚጠበቅበትን ግዴታ ማሟላት እንዲችል ነው፡፡ በአዋጁ ስለ ዓመት ፈቃድ የሚናገረው ጠቅላላ ድንጋጌ /አንቀጽ 76/2/ በዓመት ፈቃድ ፋንታ በገንዘብ መክፈል የተከለከለ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ አንድ ሠራተኛ የአመት ፈቃድ ለማግኘት ያለውን መብት በማናቸውም ሁኔታ ለመተው የሚያደርገው ስምምነት ተቀባይነት እንደሌለውም የዚሁ አንቀጽ ንዑስ /1/ ይደነግጋል፡፡ ከነዚህ ድንጋጌዎች ገንዘብ የአመት ፈቃድን መተካት እንደማይችል ሠራተኛው የአመት ፈቃዱን ባልተጠቀመ ቁጥር ፍቃዱ ወደ ገንዘብ ተለውጦ መከፈል እንደሌለበትም ያመለክታል፡፡

በሌላ በኩል በዋናነት የአመት ዕረፍት ለሠራተኛ የሚሰጠው ሳይከፋፈል ሲሆን መሰጠት ያለበትም ከእያንዳንዱ አመት የአገልግሎት ዘመን በኋላ ሳይጠራቀም ነው፡፡ /ቁጥር 77/1/ እና 78 ፡፡ ሆኖም ሠራተኛው ተከፋፍሎ እንዲሰጠው ሲጠይቅና አሠሪውም ሲስማማ ለሁለት ተከፍሎ ሊሰጠው ይችላል፡፡ /79/1/ እንዲሁም ሠራተኛው ሲጠይቅና አሰሪውም ሲስማማ በአሠሪውም በኩል የሥራ ሁኔታ ሲያስገድደው የሠራተኛውን የፈቃድ ጊዜ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡ /አንቀጽ 79/1/ እና /3/ የአመት ዕረፍትን ከላይ እንደተገለፀው በአሠሪና በሠራተኛው ስምምነት ማራዘም ቢቻልም ሊራዘም የሚችልበት ጊዜ ግን በሕጉ ወሰን ከሚቀጥለው ሁለት አመት በላይ ሊራዘም አይችልም፡፡ ይህ ድንጋጌ ከሁለት አመት መራዘም በኋላ ሠራተኛው ፍቃዱን የግድ መጠቀም ያለበት መሆኑን ያመለክታል፡፡

በመቀጠልም ሠራተኛው በዚህ ሁኔታ ተራዝሞ ያልተጠቀመበትን ፍቃድ ሁሉ የስራ ውሉ ሲቋረጥ የጊዜ ገደብ ሳይኖረው በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈለው ይችላል ወይ? ወደሚለው ጭብጥ እንመለሳለን፡፡ የአመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈልባቸው የሚችሉ ሁኔታዎች በአዋጁ በግልጽ ተቀምጠዋል፡፡ እነሱም 1ኛው የሥራ ውሉ ለተቋረጠ ሠራተኛ ሲሆን 2ኛው ደግሞ በአንቀጽ 80 እንደተገለፀው አሠሪው በፍቃድ ላይ ያለ ሠራተኛን ጠርቶ ፈቃዱን ሳይጨርስ ስራውን እንዲቀጥል ካደረገ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ በአንቀጽ 80/2/ ሠራተኛው ያልተጠቀመበትን ማለትም የቀረውን የአመት ፈቃድ በገንዘብ ተተምኖ ሊከፈለው እንደሚችል ተደንግጓል፡፡

ለያዝነው ጭብጥ አግባብነት ያለው የሥራ ውሉ የተቋረጠበት ሠራተኛን በማስመልከት ስለሚፈፀመው የአመት ዕረፍት ክፍያ ነው፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 77/5/ የስራ ውሉ የተቋረጠ ሠራተኛ ያልወሰደው የአመት ፈቃድ ታስቦ በገንዘብ እንደሚከፈለው ይደነግጋል፡፡ ከላይ እንደተመለከትነው የአመት ዕረፍት መሠረት ሃሣብ ክፍያ የሚፈፀምበት የዕረፍት ቀናት ማግኘት ቢሆንም የስራ ውሉ የተቋረጠ ሠራተኛ ግን እደደአላማው በዕረፍቱ ሊጠቀምበት አይችልም፡፡ በዋናነት የአመት ዕረፍት በገንዘብ እንዲተካ ሕጉ ባይፈቅድም በስራ ውሉ የተቋረጠ ሠራተኛ ግን በዕረፍቱ ፋንታ ገንዘብ እንዲከፈለው በህጉ ተፈቅዷል፡፡ ይህም የሆነው ከላይ እንደተገለፀው የስራ ውሉ በመቋረጡ ምክንያት ሠራተኛው በዕረፍቱ ሊጠቀምበት የማይችል በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም ክፍያ የሚፈፀምባቸው የትኞቹ ፍቃዶች ናቸው የሚለውን ነጥብ መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከትነው የአመት ፍቃድ ከሚቀጥለው ሁለት አመት በላይ ሊራዘም እንደማይችል በአንቀጽ 79/5/ ተደንግጓል፡፡ በአንቀጽ 76/1/ እና /2/ አንድ ሠራተኛ የአመት ፈቃዱን ለመተው ስምምነት ማድረግ እንደማይችል በአመት ፈቃድ ፈንታ ገንዘብ መክፈል የተከለከለ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ተገናዝበው ሲታዩ የአዋጅ አንቀጽ 77/5/ የሥራ ውሉ ለተቋረጠ ሠራተኛ እንዲከፈል የፈቀደው የአመት ዕረፍት ክፍያ ሠራተኛው ስራ ላይ ቢሆን ኖሮ ሊጠቀምባቸው የሚችሉ ፍቃዶችን እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡ ይኸውም በህጉ መሠረት ሁለት አመት የተራዘሙ ወይም ሊራዘሙ



የሚችሉና የደረሱ ፍቃዶችን ይጨምራል፡፡ ከዚህ ውጪ ግን ከሁለት አመት በላይ የተራዘሙ ፍቃዶች በገንዘብ የሚተኩ አይደሉም የሚል ድምዳሜ ላይ ያደርሰናል፡፡

ሲጠቃለል ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት አንድ ሠራተኛ የስራ ውሉ ሲቋረጥ ያልተጠቀመት የአመት ፍቃድ ክፍያ ሁሉ የጊዜ ገደብ ሳይኖረው በገንዘብ ተቀይሮ ሊከፈለው አይችልም፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት ሠራተኛው የስራ ውሉ ሲቋረጥ ያልተጠቀመበት የአመት ዕረፍት ሁሉ ያለምንም የጊዜ ወሰን ወደ ገንዘብ ተቀፋሮ9 ሊከፈለው እንደሚችል በመቁጠር የአዋጁ ቁር 42/85 አንቀጽ 77/5/ን መተርጎሙ የአመት ፈቃድ አላማንና መሠረተ ሃሣብን ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ሊታረም ይገባል፡፡

በመቀጠልም የአመት ዕረፍት ሠራተኛው በግልጽ በጽሁፍ ወይም በቃል ካልጠየቀ አሰሪውም በግልጽ እንዲተላለፍ ካልፈቀደ ፍቃዱ እንደተላለፈ አይቆጠርም ወይ? የሚለውን ጭብጥ እንመለከታለን፡፡ የአዋጁን አንቀጽ 79/2/ የአመት ፈቃድ ሠራተኛው ሲጠይቅና አሰሪውም ሲስማማ ሊተላለፍ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ የአመት ፍቃድን ለማስተላለፍ የአሰሪውና የሠራተኛው ስምምነት አስፈላጊ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ስምምነት በግልጽ ወይም ግልጽ ባልሆነ መንገድ ሊደረግ ይችላል፡፡ ስምምነት ከአሠራርም ሊታይ ይችላል፡፡ ሠራተኛው በስምምነት እንኳን ሊተወው የማይችል የአመት ዕረፍት በሕግ ተሰጥቶታል፡፡ ፍቃዱን መጠቀሙ መብቱም ግዴታውም ነው፡፡ አሠሪው ኘሮግራም አውጥቶ ለሠራተኛው ፍቃድ መስጠት እንዳለበት የአዋጁ ቁጥር 78/2/ ይደነግጋል፡፡ የአመት ዕረፍትን ለተወሰነ ጊዜ ማራዘም እንደሚቻል ከላይ በ1ኛው ጭብጥ ተመልክተናል፡፡ እንግዲህ ሠራተኛው ፍቃድ መውሰድ ባለበት ጊዜ ሳይወስድ ቢቀር አሰሪውም ሳይሰጠው ስራውን እንዲቀጥል ቢያደርግ ከአሠራራቸው ፍቃዱን ለማራዘም የተስማሙ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ስምምነቱም ፍቃዱ በሕግ እንዲራዘም እስከተፈቀደ ጊዜ ድረስ ብቻ እንደተደረገ ሊቆጠር ይገባል፡፡

ሲጠቃለል ፍቃድን ለማስተላለፍ የሚደነግገው አዋጁ ድንጋጌ /አንቀጽ 79/ ፍቃድን ለማስተላለፍ አሰሪውና ሠራተኛው መስማማት ያለባቸው መሆኑን

ቢያስገነዝብም ስምምነታቸው ግን ግዴታ በግልጽ መሆን እንደሚገባው የግልጽነት ፎርማሊቲን እንዲያሟላ አያስገድድም፡፡ ስምምነት መኖሩን ደግሞ ከአሠራር መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም አመልካች ፍቃድ ተላልፏል ለማለት አሰሪውና ሠራተኛው የግድ በግልጽ መስማማት አለባቸው የሚለው ክርክሩ ተቀባይነት የለውም፡፡

**ውሣኔ**

1. ተጠሪ ወደ ገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈለው የጠየቀው የአመት ዕረፍት ቀናት ክፍያ ሁሉም ሊከፈለው አይገባም፡፡
2. ተጠሪ የ1984፣ የ1985 እና የ1996 ከስራ አስከተሰናበተበት እስከ ጥር 30 ድረስ ያለው የአመት ዕረፍት በገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈለው፡፡
3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በስራ ክርክር መዝገብ ቁጥር 1438 ነሐሴ 16 ቀን 1994 ዓ.ም እንዲሁም የከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 15313 ህዳር 25 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348/1/ መሠረት ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡



**የመ/ቁ.** 16270

*ታህሣሥ* 17 **ቀን** 1998 **ዓ.ም**

**ዳኞች፡-** አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ሐጐስ ወልዱ

አቶ ዳኜ መላኩ

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

**አመልካች ....** አዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት

**ተጠሪ.....** አቶ መሐሪ ማታ

*ከውል ውጪ ያለ ኃላፊነትን በተመለከተ ስለ ካሳ መካስን አወሳሰን*

*የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2066(2)፣ 2086(2)፣ 2081፣ 2090፣ 2091 2102(1) እና 2092*

የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽ የሆነው የአሁን አመልካች መኪናው አድርሷል በተባለው የግጭት አደጋ ለተጎዷው የጉዳት እና መራል ካሳ እንዲሁም የህክምና ወጪ በድምሩ ብር 30.198 እንዲከፍለው በመወሠኑ እና የደቡብ ብሔር ብሔረሠቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔውን በማፅናቱ የቀረበ አቤቱታ

<u>ውሳኔ፡ -</u> የደቡብ ብሐር ብሐረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሠጠው ውሳኔና የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ፀድቋል፡፡

1ኛ. ከውል ውጪ ኃላፊነት በሆነ ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳቱ የደረሰው በተከሳሹ መኪና መሆኑን ከማስረዳት ውጪ በባለሀብቱ በኩል ጥፋት ስለመኖሩ ማረጋገጥ አይጠበቅበትም፡፡

2ኛ ጥፋት ባይኖርም በኃላፊነት ተጠያቂ የሆነ ሰው ከኃላፊነት ነፃ ለመሆን ጉዳት የደረሰበትን ሠው ሌላ የወንጀል ድርጊት ለመጥቀስ አይችልም፡፡

3ኛ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 343(1) መሠረት ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተመልሶ ከተላከ ፍርድ ቤቱ በመጀመሪያው ውሳኔ ሳይገደብ የካሳውን መጠን ሊያሻሽል ይችላል፡፡